# በገና ወይም በጌታ ልደት በዓል ስጦታ የመስጣጠት ባሕል የኛ ወይስ የሌላ?



ምዕራባዊያን ለገና ማለት ለጌታችን ለአምላካችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል እርስ በእርሳቸው ስጦታ የመሰጣጣት በጣም ጥሩና ደስ የሚል ባሕል አላቸው፡፡ ይሄ ባሕላቸውም የጥበብ ሰዎች (ሰብአ ሰገል) ወይም የምሥራቅ ነገሥታት ጌታ በተወለደ ጊዜ ለጌታ ያበረከቱትን የወርቅ የዕጣን የከርቤ ስጦታን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

እንግዲህ ነጥቡ ያለው እዚህ ላይ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ከመወለዱ በፊት ጌታ እንደሚወለድና በተወለደ ጊዜም እነኝህ ነገሥታት እጅ መንሻ እንደሚያቀርቡለት ጌታ ከመወለዱ ከሽህ ዓመታት በፊት ጀምሮ በትንቢት ተነግሮ ነበር፡፡ አንዱን ብንጠቅስ፡-

"በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ። የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ። ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል። አሕዛብም ሁሉ ይገዙለታል" መዝ. 72፤ 9-11

በትንቢቱም መሠረት በማቴ. 2፤1-11 ላይ እንደተገለጸው ትንቢቱ ተፈጽሟል፡፡ በዚህ ጥቅስ ላይ ስለእነዚህ ነገሥታት የተጻፈውን ስናይ ነገሥታቱን "የምሥራቅ ነገሥታት" ሲል ይጠራቸዋል፡፡ ነቢዩ ልበ አምላክ ዳዊት ስለ ነገሥታቱ አስቀድሞ በትንቢት ከተናገረው ቃል ጋር በማቴዎስ ወንጌል ላይ ነገሥታቱ የምሥራቅ ነገሥታት መሆናቸውን ከተናገረው ቃል ጋር ስናገናዝብ "የምሥራቅ" የሚለው ቃል የግብር (በቤተክርስቲያን ተምሳሌታዊ አገላለጽ ምሥራቅ የጽድቅ፣ የምሕረት፣

የሕይወት ተምሳሌትነት አለው) እናም “የምሥራቅ” ተብሎ መጠቀሱ ከነገሥታቱ ተግባርና አገልግሎት አኳያ የዚህ ተምሳሌታዊ አገላለጽ መግለጫ እንጅ የአቅጣጫ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም ነገሥታቱ ከመጡባቸው የተጠቀሱ ሀገራትን የወሰድን እንደሆነ ተርሴስ ያለችው ከኢየሩሳሌም ወይም ከእስራኤል በስተምዕራም በኩል እንጅ በስተምሥራቅ በኩል አይደለችምና፡፡ ተርሴስ ብቻም ሳትሆን ኢትዮጵያም (ሳባም) ዓረብም ያሉት ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ እንጅ በስተ ምሥራቅ በኩል ስላልሆነ፡፡

የቤተክርስቲያን መጻሕፍት ስለእነዚህ ነገሥታት ታሪክ በዝርዝር ጽፈዋል፡፡ የታሪክ ጸሐፍትም እንዲሁ፡፡ አንዳንዶቹ መረጃዎች እንደሚሉት አንደኛው ንጉሥ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ሁለቱ ነገሥታት ግን በእርሱ ስር ያሉ እሱ የሾማቸው የግዛቱ ነገሥታቶች እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ ሌላው ቢቀር ግን ከሦስቱ አንዱ ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ መረጃውም አንዱ ከላይ የጠቀስኩት የመዝሙረኛው ዳዊት ጥቅስ ሲሆን ሌላኛው ትውፊታዊ መረጃዎች ናቸው፡፡ ትውፊታዊ መረጃን መሠረት አድርጎ የተሣለ ይሄ ኢየሩሳሌም ያለ ጥንታዊ ሥዕል ራሱ የሚያረጋግጠው ይሄንኑ ነው፡፡ በዚህ የምዕራባዊያን ሥዕል አንደኛው ንጉሥ ኢትዮጵያዊ (ጥቁር) ሆኖ ተሥሏልና፡፡

እዚህ ላይ “መጽሐፍ ቅዱስ ሳባ ብሎ ሲል ኢትዮጵያን ሳይሆን ዓረብን ነው” የሚሉ አሉና ለእነሱ ልንላቸው የምንችለው ነገር ቢኖር ሳባ ማለት ዓረብ ቢሆን ኖሮ ይህ የመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ ሳባ ካለ በኋላ ዓረብ ብሎ ሌላ ባልጠራ ነበር፡፡ እርግጥ ነው ንግሥት ሳባ የዓረብን ምድር የገዛች ንግሥት ስለሆነች ዓረቦች እንደራሳቸው ንግሥት ይቆጥሯታል ከዚያም አልፈው የእኛ ናት እንጅ የኢትዮጵያ አይደለችም ይላሉ፡፡

የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ንግሥተ ሳባ የዓረብ ናት ብለው የሚሉ ሰዎች ንግሥተ ሳባ የኢትዮጵያ ንግሥት እንደሆነች የሚናገረውን መጽሐፍ ክብረ ነገሥትን የጻፉት ዓረቦች ናቸው ማለታቸው ነው፡፡ እንደዛ ከሆነ ዓረቦቹ እራሳቸው ንግሥተ ሳባ የኢትዮጵያ ንግሥት መሆኗን መስክረዋል ማለት ነዋ! ደግሞስ እንዴት ጅል ቢሆኑ ነው “ዓረቦች ታሪካቸውን እንካቹህ ውሰዱት ድመቁበት እኛ ይቅርብን” ብለው የሚያስረክቡት?

የመጽሐፍ ቅዱስን መረጃ በመዳሰስ ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት መሆኗን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጠቀሱት እንደሌሎች ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊ ተብሎ እንደተጻፈው ሁሉ ሳባንም “ኢትዮጵያዊት” ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ አልጠራም፡፡ በአንጻሩም የመናዊት ወይም ዓረባዊትም አላላትም፡፡ እነኚህን ባይልም ዜግነቷን ወይም ሀገሯን በቀላሉ ልንለይ የምንችልበት ቀላል መንገድ ግን አለ፡፡

እንደሚታወቀው እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሀገርና በሕዝብ በመንግሥትም ደረጃ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ወይም የሚያውቁ እሱም የሚያውቃቸውና ሕዝቤ ልጆቼ የሚላቸው ሕዝቦች ወይም ሀገሮች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ እነርሱም ኢትዮጵያና እስራኤል ከእነዚህ ውጪ ማንም አልነበረም፡፡ ሌሎች ሀገሮች ከተነሡም በስደት ሔደው ምኩራባቸውንም በዚያ ሠርተው እግዚአብሔርን ያመልኩ ከነበሩት አይሁዳውያን የተነሣ ካልሆነ በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ከእስራኤል ልጆችና ከኢትዮጵያ ልጆች ውጪ እግዚአብሔርን ያመልካሉ ተብሎ የተጻፈለት ሕዝብ አልነበረም፡፡ በት.አሞ.፱፥፯ ላይ እማ እንዲያውም በኩራት (የመጀመሪያ) ናቸው ከሚባሉት እስራኤላዊያንም ይልቅ እኛ ኢትዮጵያዊያኑ ከብረን እንታያለን፡፡ ቃሉ እንደሚለው “የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር”፡፡ እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆችን እንደእኛ የኢትዮጵያጵያ ልጆች አድርጐ እንደሚያያቸው ከእኛ አሳንሶ እንደማያያቸው የእስራኤል ልጆችን በማጽናናትና በማረጋጋት የተናገረበት ጊዜ ነበር፡፡

እንግዲህ ቁልፉ ነገር ያለው እዚህ ላይ ነው፡፡ ሳባ በእግዚአብሔር የምታምን እንደነበረች ከተናገረችው ቃል መረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛ ነገሥት 10፤1-13 ሁለተኛ ዜና መዋዕል 9፤1-12 ላይ ታሪኩ ተጽፎ እንደሚገኘው ሳባ ሰሎሞንን “አንተን

የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፡፡ እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘለዓለሙ ወዶታልና፡፡ ስለዚህ ጽድቅና ፍርድን ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጐ አስነሣህ" ብላዋለች፡፡

በንግግሯ እግዚአብሔር የጽድቅና የፍርድ አምላክ መሆኑን አስቀድሞ ከነበራት እምነት ተነሥታ መስክራለች፡፡ የተባረከ ይሁን ብላም ፈጣሪዋን አመስግናለች፡፡ ይሄንን ንግግር ለመናገር ስለእግዚአብሔር ጥልቅ የሆነ እውቀትና እምነት ጊዜ የወሰደ ትውውቅ ሊኖራት ግድ ይላል፡፡ ከእስራኤላዊያን ውጪም ይህንን ሊያደርጉ የሚችሉ ሌላ ሕዝብና መንግሥት ካለም ቀደም ሲል በቀረበው ማብራሪያ ወይም በመጽሐፍ ቅዱሱ መረጃ መሠረት ኢትዮጵያዊያን ብቻ ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ከሳባም በፊት ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን የምታመልክ ሀገር መሆኗን የሚያረጋግጡ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች አሉ፡፡

እስራኤላዊያን ከሌላ ከማንም ወገን ጋር እንዳይጋቡ በእግዚአብሔር ተከልክለው በነበሩበት ወቅት ጭራሽ ሊቀነቢያት ሙሴ ግን ያገባው ኢትዮጵያዊቷን የካህንኑ የራጉኤልን (የዮቶርን) ልጅ ሲፓራን ነበር፡፡ ይህንን በማድረጉም ከእግዚአብሔር ዘንድ አንዳችም ተግሳጽ አልደረሰበትም፡፡ ይልቁንም ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን በማግባቱ ያጉረመረሙት ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም እግዚአብሔር በባሪያዬ በሙሴ ላይ አጉረምርማችኋል በማለት ቁጣውን አወረደባቸው ማርያምንም በለምጽ ቀጣት እንጂ፡፡ ዘኁ.፲፪፥፩-፲፭ ዘጸ.፪፥፲፮-፳፪ ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሎች ነቢያት ወደኋላ ግልጽ እንዳደረጉት የኢትዮጵያ ሕዝብ እግዚአብሔርን አምላኪና ሕዝበ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው፡፡

ክብረ ነገሥት የሳባ አባቶች ዘንዶ አምላኪ እንደነበሩ ይናገራል፡፡ ይሄ ማለት ግን እግዚአብሔርን ጨርሶ አያውቁትም ነበር ማለት አይደለም፡፡ እስራኤላውያንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ያ ሁሉ ተአምራት እየተደረገላቸውና እያወቁት ለጣኦት ያልሰገዱበትና ጣኦት ያላመለኩበት ዘመን አልነበረምና፡፡ ከነገሥታቶቻቸውም ከዳዊት በስተቀር ለጣኦት ያልሰገደ አልነበረምና፡፡ እንዲህ በመሆናቸው ግን እግዚአብሐየርን ጨርሶ የማያውቁ እንደሆኑ አላስቆጠራቸውም፡፡ እኛም ላይ እንደዛው ነው፡፡

እናም ተታለው ተወናብደው ጥልቅና ጠንቃቃ ንባብና መረዳትም ከማጣት የተነሣ ክብረ ነገሥትን የፈጠራና የተረት መጽሐፍ አድርገው ለሚያዩ እንዲታይም ለሚጥሩ ግለሰቦች ከላይ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ለመግለጽ ከሞከርኩት መረዳት እንደሚቻለው ሁሉ ክብረ ነገሥት ንግሥተ ሳባን ኢትዮጵያዊት መሆኗን አረጋግጦ ታሪኳን ሲተነትን ፈጥሮ አይደለምና ተረት ፈጠራ አለመሆኑን ሊያውቁ ይገባል፡፡ ይሄንን የሚጠራጠሩ ሰዎች ናይጄሪያ ቢሔዱ የንግሥተ ሳባን አፈ ታሪክ ሊሰሙ ይችላሉ ግዛቷ እንደነበረም ሊነግሯቸው ይችላሉ፡፡ ከሀገሯ ስትመጣ የመጣችበት ነው የሚሉትን የዋሻ መንገድም ሊያሳዩዋቸው ይችላሉ፡፡ የመኖች ንግሥተ ሳባን የኛ ንግሥት ናት የሚሉበት ምክንያትና የግእዝ አሻራዎችም እዛ የመገኘታቸው ምክንያት ከጥንት ዘመን ጀምሮ እኛ ከፋርሶች ጋር በመፈራረቅ ሳውዲ ዓረቢያንና የመንን ለረጅም ጊዜ ስንገዛው ስለነበረ ነው እንጅ ሳባ ዓረብ ስለነበረች አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የመንን እንደገዛች ደግሞ እራሳቸው የመኖችም የሚያረጋግጡት ነገር ነው፡፡

ሌላኛው የሚያከራክር ነጥብ ደግሞ እነዚሁ በምዕራባዊያን የታሪክ ቀበኞች የተወናበዱ ዜጎቻችን "አይ! መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚላት የምድያምን አሁን ሱዳን ተብሎ የሚጠራውን ምድር ነው እንጅ ኢትዮጵያን አይደለም" ይላሉ፡፡ እንዲህ

ለሚሉ ግለሰቦች የምለው ነገር ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ "ኢትዮጵያ" ብሎ ሲል በእርግጥ ግዛቷ የምድያምን ምድር ጨምሮ ሰፊ የነበረ ቢሆንም እምብርቷ ግን ይህቺ አሁን ያለችው ኢትዮጵያ መሆኗን ሲያረጋግጥ "የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው፡፡ እሱም የኢትዮጵያን ምድር ይከባል" ዘፍ. 2፤13 ብሎ ግዮን ወይም ዓባይ በምድሯ መንጭቶ ምድሯን የሚያካልላት ምድር

መሆኗን በመናገር የኢትዮጵያን መልክዓምድራዊ አድራሻ (Geographical location) የት እንደሆነ ቁጭ አድርጎታልና መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ ብሎ ሲል የጥንት ግዛቷ ሰፊ የነበረ ቢሆንም ይህችን ኢትዮጵያችንን ማለቱ እንደሆነ ያለጥርጥር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ስለሆነም ወደቀደመው ነገራችን እንመለስና በዚህም መሠረት ጌታ ሲወለድ እጅ መንሻ ካቀረቡ ነገሥታት ውስጥ ከበዛ ሦስቱ ካነሰ አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደነበር እርግጠኛ መሆን ይቻላል ማለት ነው፡፡

እንግዲህ ምዕራባዊያኑ በጌታ ልደት በዓል እርስ በእርሳቸው ስጦታ የመሰጣጣት ባሕሉን የወሰዱት ወይም መሠረት ያደረጉት የጥበብ ሰዎችን ወይም ለጌታ የወርቅ የዕጣን የከርቤ እጅ መንሻ ያቀረቡትን ነገሥታት እንደሆነ ይናገራሉና ይህ ስጦታ የመሰጣጣት ባሕላቸው ፈጣሪ እኛ ነን ባሕሉም የእኛ እንጅ የእነሱ አይደለም ማለት ነው፡፡ እናም በጌታ ልደት በዓል ስጦታ የምትሰጣጡ ወገኖች ካላቹህ ይህን ውብ ባሕል ስታደርጉ የራሳቹህን ባሕል እንደፈጸማቹህ በማሰብ አድርጉት እንጅ የተውሶ ባሕል እያደረጋቹህ እንደሆነ እንዳይሰማቹህ እንዳታስቡ ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

እንኳን አደረሳቹህ! በዓሉን የነጻነት፣ የይቅርታ፣ የምሕረት፣ የረድኤት፣ የበረከት፣ ያድርግልን! አሜን!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com